# ሰላማዊ (Non-violent) ትግል

መክብብ ማሞ

## እንደ መነሻ

የዚህ አጭር መጣጥፍ ዋና መነሻ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ «ያለፈውንና ያለንበትን አይቶ የወደፊቱን አቅዶ መንቀሳቀስ»[1] በሚል ርዕስ ባቀረቡት ጽሑፍ ላይ በመመርኮዝ ሲሆን በተለይ በጽሑፉ ማጠቃለያ ላይ ሁላችንም የበኩላችንን ሃሳብ እንድናቀርብ ባስገነዘቡት መሠረት እኔም የበኩሌን ልሰንዝር ከሚል ሃሳብ የተጻፈ ነው:: ሌላው በዚህ ጽሁፍ ውስጥ በተወሰነ መልኩ ሃተታ የተሰጠበት ክፍል አቶ አንዳርጋቸው ከዘረዘሯቸው አራት ነጥቦች መካከል በተለይ በአራተኛው ክፍል ላይ «የድርጅቱ የወደፊት አቅጣጫዎችን» በተነተኑበት ክፍል ካነሷቸው አንዳንድ ነጥቦችን መካከል እኔም ያለኝን ሃሳብ ለመጠቆም ነው:: በመጨረሻም በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በሰላማዊ ትግል ዙሪያ ጠቅለል ያሉ ሃሳቦችን ለመዳሰስ ሙከራ የተደረገ ሲሆን ባገራችን ካለው ሁኔታ በመነሳት በውጪ ያለው ኢትዮጵያዊ ሚና ምን መሆን እንዳለበት የተወሰኑ ሃሳቦችን ለመጠቆም ሙከራ ተደርጓል::

## ሰላማዊ (Non-violent) ትግል

በትርጉም ግድፈትም ይሁን ወይም ተስማሚ ቃል ባለማግኘት በተለምዶ «የሰላማዊ ትግል» እየተባለ የሚጠራው በእንግሊዝኛ Non-violent/Non-violence ከተሰኘው ቃል የተወሰደ ሲሆን ባማርኛችን የተሰጠው መጠሪያ የእንግሊዝኛው ቃል ቀጥተኛ ትርጉም ሳይሆን የቃሉን አጠቃላይ ይዘት በማጤን የእንግሊዝኛው ቃል ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልዕክት ተመርኩዞ የተፈጠረ የቃል አጠቃቀም ይመስላል:: ለዚህም ሊሆን ይችላል «የሰላማዊ ትግል» ሲባል ለብዙዎች የተለያየ አንዳንዴም የተመሰቃቀለ ትርጉም ያለው:: የሆነው ሆኖ የቋንቋ መሠረታዊ ዓላማ ለመግባቢያነት ማገልገል ስለሆነና ባሁኑ ጊዜ እየተጠቀምንበት ያለው ይኸው ቃል በመሆኑ እኔም በዚህ ጽሁፍ ውስጥ በዚሁ ቃል መጠቀምን መርጫለሁ::

በመሠረቱ የሰላማዊ ትግል አመጽን ፣ ጥላቻን ፣ ክፋትን ፣ ደም መፋሰስን ፣ ቂም በቀልን ወዘተ ባሕርያትን በመቃወም ላይ ያተኮረ ትግል ነው:: የሰላማዊ ትግል አራማጆች ለአንድ ማኅበረሰብ ለማምጣት የሚፈልጉት ለውጥ ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ውጪ ሰላማዊና መልካምነትን መሠረት ባደረገ መንገድ ነው:: ከዚህ በፊት በታሪክ እንደታየውና ባሁኑ ጊዜም በተለያየ ያለማችን ክፍል በዚህ ትግል ውስጥ ያሉ እንደሚያራምዱት በሰላማዊ ትግል የሚመጣ ለውጥ ዘላቂነት ያለው ፣ በአንድ አገር ውስጥ ያለውን ውስብስብ ችግር ከመፍታት አኳያ ከተለያዩ የትግል አካሄዶች መካከል የተሻለ አማራጭ እንደሆነ መገንዘብ አያዳግትም:: ሆኖም ግን የትግሉን ጥልቀት ካለመረዳትም ይሁን ከተለመደው የፖለቲካ አካሄድ ወጣ ከማለቱ የተነሳም ሊሆን ይችላል የሰላማዊ ትግል ለብዙዎች በተለይም ለፖለቲካ ልሒቃን ብዙም ጆሮ የሚሰጡት ጉዳይ ካለመሆኑ ባሻገር አንዳንድ ጊዜ «የተራ ሰዎች ፖለቲካ» እየተባለ ሲጠራ የምንሰማው:: ሆኖም ግን የሰላማዊ ትግል ሊያቋቁም የሚታገለው ሥርዓት ግልጽነትና የሰላምን መሠረት የተከተለ በመሆኑ እንደዚህ ዓይነት ሥርዓትን ለመፍጠር የሚጠቀምበት መንገድም ወደፊት ለማስፈን ከሚሻው ሥርዓት የሚለይ አይደለም:: ይህንን አስመልክቶ ዶ/ር ኪንግ እንዲህ ብሏል:- **". . . nonviolence demands that the means we use must be as pure as the ends we seek."**

ከዚህ አኳያ ከተመለከትነው የሰላማዊ ትግል የደካሞች ትግል ወይም የምስኪኖች ትግል አይደለም:: ሰላማዊ ትግል የልመናም ትግል አይደለም:: ይልቁንም የሰላማዊ ትግል

---

[1] http://www.kinijitethiopia.org/docs/articles/Kinijit_past_present_future_andargachew_tsege.pdf

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ሰዎች ወደዚህ ምድር በሚመጡበት ጊዜ ከፈጣሪ የሚሰጣቸውን ልዩ የሆነና ማንም ሊገስሰው የማይችልን መብት «የኔ ነው» ብሎ የመታገያ መንገድ ነው:: እነዚህ መብቶች ገዢዎች እንደፈለጉ ለማንም የሚሰጡትና ማንንም ሲሻቸው የሚነፍጉት ሳይሆን እያንዳንዳችን «እነዚህ የኔ መብቶች ናቸው ፤ አትንኩብኝ» ብለን የምንታገልላቸው ናቸው:: በተለያየ ጊዜ በሥልጣን ላይ የሚቀመጡ መንግሥታት እነዚህን መብቶች ባገኙት አጋጣሚ የሚሸራርፉ ብለውም የሚነጥቁ ቢሆንም እኛ ግን እነዚህን የተነጠቅናቸውን መብቶች መልሰን የምናስከብረው ከገዢዎች በምናገኘው ችሮታ ወይም የእነርሱን መልካም ፈቃድ በመጠየቅ ሳይሆን እነዚህን መብቶቻችንን በምናገኘው አጋጣሚ ሁሉ "claim" በማድረግ ነው::

በታሪክ ከዚህ በፊት የተደረጉ የሰላማዊ ትግሎችን በምናጤንበት ጊዜ አንድ የምንገነዘበው ሃቅ ትግሉ ከራስ የሚጀምር መሆኑን ነው:: በውስጣችን ያለውን ጥላቻ ፣ የበቀል ስሜት፣ አጋጣሚን ጠብቆ ጠላት ብለን የምንፈርጀውን ለማጥቃት መፈለግ ፣ ሕጋዊ ጠለላዎችን በመመርኮዝ በጠላታችን ላይ እርምጃ ለመውሰድ ማሴር . . . . የመሳሰሉ ስሜቶችን አስቀድሞ ከመታገል ይጀምራል:: ምክንያቱም «ጠላት» ለምንለው አካል እንኳን ተገቢውን በሕግ የመዳኘት ዕድል ሰጥተን ፍትሕ እንዲበየን ለማድረግ አስፈላጊውን እናደርጋለን እንጂ «ደግሞ ላንተ ሕግ መጥቀስ» በሚል ነጻ እርምጃ አንሰወድም:: ወደፊት ለመመስረት የምንታገልለትን የፍትሕም ሆነ የዴሞክራሲ ሥርዓት ገና በትግሉ ወቅት ባግባቡ መለማመድ መቻል አለብን:: ይህም ልምምድ በየጊዜው ከምንመለከተው ኢ-ፍትሐዊነት የተነሳ አውቀነውም ሆነ ሳናውቅ ቀስ እያለ ሥር እየሰደደ የሚመጣን የጥላቻን ሃሳብ መዋጋት በተለይ የሚያካትት ነው:: ለዚህም ነው ዶ/ር ኪንግ ይህንን የተናገረው:-

> "**Non violence means avoiding not only external physical violence but also internal violence of spirit. You not only refuse to shoot a man, but you refuse to hate him.**"

ወደ ዋናው ጉዳይ ስመለስ ፤ ከላይ እንደገለጽኩት አቶ አንዳርጋቸው በጽሁፋቸው ካስቀመጡት ነጥቦች መካከል በገጽ 23 ላይ በተለይ በኢትዮጵያ ስለሚደረገው ሰላማዊ ትግል አስመልክቶ ሲናገሩ:-

> «. . . በኢትዮጵያ የሚደረግ ሰላማዊ እና ህጋዊ ትግል . . . ህንድን ከእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ነጻ ለማውጣት በማህተመ ጋንዲ እንደተመራው የሰላማዊ የነጻነት እንቅስቃሴ ጋር በማመሳሰል ከፍተኛ ስህተት ከመስራት መቆጠብ ይኖርብናል::» ካሉ በኋላ ምክንያቱ ሲጠቅሱ «ህንድ በእንግሊዝ ቅኝ ግዛትነቷ የእንግሊዝ አካል ስለነበረች የእንግሊዝ የፖለቲካ ሥርዓት የደረሰበት የዕድገት ደረጃ . . . (ለ)ማህተመ ጋንዲ ሰላማዊ ትግል ማድረግ እንዲችል በጣም የተመቻቻ ሁኔታ እንደፈጠሩለት(ና) . . . (ይህም መሆን የቻለው) የህግ የበላይነት የሰፈነበት ፣ የፖለቲካ ባለሥልጣናቱ የሚያስተላልፉትን **ህገወጥና ኢ-ሰብዓዊ ትዕዛዝ ላለመፈጸም በራስ መተማመኑ ፣ ድፍረቱ ፣ እውቀቱና ብቃቱ ባላቸው ከፍተኛ የወታደራዊና የፖሊስ መኮንኖች** ባሉበት አገር ውስጥ እንደሆነ ልብ ማለት ይገባል»[2] ብለዋል::(ያቀለምኩት እኔ ነኝ)

ታሪክስ ስለዚህ ምን ይላል?

[2] http://www.kinijitethiopia.org/docs/articles/Kinijit_past_present_future_andargachew_tsege.pdf

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

## ጋንዲ በአገረ ሕንድ

በልጅነትና በወጣትነት ዘመኑ ሁሉ በኮሳሳነቱና በደካማነቱ የሚታወቀው ሞሐንዳስ ጋንዲ ከአያቱ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን የፖረባንዳር ግዛት ጠቅላይ ሚኒስትርነት ተረካቢ እንዲሆን ከቤተሰቡ በተደረገበት ግፊት ምክንያት የሕግ ትምህርት ለመከታተል ወደ እንግሊዝ አገር የሄደው በወጣትነት ዕድሜው ነበር፡፡ ምንም እንኳን በጉዞው አጎቱ ባይስማሙም ከመሄዱ በፊት እንግሊዝ አገር በሚቆይበት ወቅት በሙሉ «ወይን ላለመጠጣት ፣ ሴት ዘንድ ላለመቅረብ እና ሥጋ ላለመብላት» ቃለ መሃለ ከፈጸመ በኋላ ጉዞውን ወደዚያው አቀና፡፡

ጋንዲ በእንግሊዝ አገር ኮሌጅ ትምህርቱን አጠናቅቆ ወደ ህንድ እንደተመለሰ ያሰበው ነገር በሙሉ አልሆነም፡፡ በዚህም ምክንያት በሰለጠነበት የሕግ ሙያ ለመሥራት ወደ ደቡብ አፍሪካ ተጓዘ፡፡ እዚያም ብዙ ሳይቆይ መላ ህይወቱ የሚቀይር እና ፈጽሞም ወደ አላሰበው አቅጣጫ ህይወቱን የሚመራ ድርጊት ተከሰተ፡፡

የጋንዲን በአካል መገኘት የሚሻ አንድ የክስ ጉዳይ ስለነበር ጋንዲም ይህንኑ ለማስፈጸም ወደ ፕሪቶሪያ ያመራል፡፡ በምሽቱ ባቡር የአንደኛ ማዕረግ ትኬት አስቆርጦ ጉዞውን ያቀናል፡፡ ናታል በተሰኘችው ግዛት ሲደርስ ለነጮች ብቻ በተፈቀደው ክፍል «ጠጉረ ልውጥ» መቀመጡን የተመለከተ አንድ ነጭ የባቡሩን ሃላፊዎች አስከትሎ በመምጣት ወደ ሶስተኛ ማዕረግ እንዲሄድ ለጋንዲ ትዕዛዝ ይሰጡታል፡፡ ትዕዛዙን የተቃወመው ጋንዲም ትኬቱን በማሳየት ወደሌላ ማዕረግ ለመሄድ ፈቃደኛ አለመሆኑን በአጽንዖት አረጋገጠ - በመቀመጥም ተቃውሞውን ገለጸ፡፡ በሁኔታው የተናደዱት ኃላፊዎች ፖሊስ ወደ ባቡሩ ክፍል እንዲመጣ በማድረግ ጋንዲን ከነሻንጣው አሽቀንጥረው ወደ ፌርማታው መጠለያ ይወረውሩታል፡፡ ይህ ሁኔታም በወደፊቱ የጋንዲ ማንነት ላይ የመጨረሻውን ለውጥ ያመጣ የመጀመሪያ ክስተት ሆነ፡፡

በደቡብ አፍሪካ ስለሚኖሩ ህንዳውያን መብት በመቆም ከፋፋዩን የአፓርታይድን ሥርዓት በመዋጋት ትግሉን የጀመረው ጋንዲ ፧ ለዓመታት ብዙ መከራ እና ግፍ ከተቀበለ በኋላ በአገሩ ህንድ የተንሰራፋውን የእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ለመታገል ጉዞውን ወደ ህንድ አቀና፡፡ በእንግሊዝ አስተዳደር ከፍተኛ ምሬት ውስጥ የነበረውንና በሃይማኖት ተከፋፍሎ የቆየውን የህንድ ህዝብ ወደሰላማዊ ትግል ለማምጣት ጋንዲ ራሱን ከምስኪኖቹ ህንዳውያን እንደ አንዱ ከማድረግ ጀምሮ ለረጅም ቀናት ራሱን ከምግብ እስከማቀብ ድረስ መራራ ትግል አካሂዷል፡፡ በኋላም የህይወት መስዋዕትነት እስከመክፈል ድረስ ራሱን አሳልፎ ሰጥቷል፡፡ «ጸሃይ የማትጠልቅባትን የታላቋን ብሪታንያ» የግፍ አገዛዝ ከአገሩ በሰላማዊ ትግል ለማስወጣት ያልተጠቀመው አማራጭ ፣ ያልተጓዘው መንገድ አለ ለማለት አዳጋች ይሆናል፡፡ በአጸፋው የእንግሊዝ አስተዳደር የጋንዲን ሰላማዊ ትግል በጸጋ የተቀበለበት አንድም ጊዜ አልነበረም፡፡ በዘመናችን ከተፈጸሙ አሰቃቂ ድርጊቶች መካከል በዘግናኝነቱ ታሪክ ሲያስታውሰው የሚኖረውን የአምሪትሳር ዕልቂት (Amritsar Massacre) መመልከቱ ብቻ የጋንዲን ሰላማዊ ትግል መራራነትና እልህ አስጨራሽነት እንዲሁም በሰው አገር የፈለጉትን ለማድረግ ያልተገደበ መብት እንዳላቸው ያለአንዳች ሃፍረት ያሳዩትን የእንግሊዝ የፖለቲካና የወታደር/ፖሊስ ባለስልጣናት ጭከና የሚያሳይ ጉልህ ማስረጃ ነው፡፡

ዕለቱ እሁድ ሚያዚያ 13 1919 ዓ.ም.[3] ነበር፡፡ ዓመታዊውን የህንዶች ክብረ በዓል ለማክበር ሴቶች ፣ ህጻናት ፣ ወጣቶችና አረጋውያን ተሰብስበዋል፡፡ ይህ በዓል ከመከበሩ ከጥቂት ቀናት በፊት ባጠቃላዩ የፑንጃብ ግዛት «የእንግሊዝ አስተዳደርን ለማስወገድ የተቀነባበረ ሴራ» አለ በሚል ግዛቱ ባጠቃላይ ውጥረት ሰፍኖበት ነበር፡፡ ከዚህም ጋር

---

[3] በተለይ እስካልተጠቀሰ ድረስ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ያሉት ቀናት በሙሉ እንደ አውሮጳውያኑ ቀመር ነው፡፡

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

በተያያዘ እንግሊዛዊው የግዛቱ ምክትል ገዥ ተጠርጣሪዎች እንዲያዙና ወደሌላ ግዛት እንዲባረሩ የሰጡት ትዕዛዝ የበለጠ ውጥረቱን አባብሶት ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ አንዲት የትምህርት ቤት ሃላፊ እንግሊዛዊት ንዴት በሞላባቸው አድመኞች ጥቃት ተሰንዝሮባት ባካባቢው በነበሩ ህንዳውያን እርዳት ልትተርፍ ችላ ነበር። የዚህ ሁሉ ሁኔታ ውጥረቱን ያባባሰው ቢሆንም ሁኔታውን ወደጎን በመተው ነበር ሰላማዊ የሃይማኖት በዓላቸውን ለማክበር ህንዳውያኑ የተሰበሰቡት።[4] በወቅቱ የተሰበሰቡበት ቦታ ዙሪያው በአጥር የተከበበና አምስት በሮች የነበሩት ሲሆን አራቱ በጣም ጠባብ ከመሆናቸው የተነሳ ቁጥሩ የተወሰነን ሰው ብቻ ነበር ማሳለፍ የሚችሉት። አምስተኛው ደግሞ በታጠቁ ወታደሮችና አውቶማቲክ ጠብመንጃ በተደገነበት ሁለት ወታደራዊ መኪና ተዘግቶ ነበር። ቀጥሎም ባካባቢው ከተሰማሩት ዘጠና ወታደሮች መካከል ወደ መሰብሰቢያው ቦታ የገቡት ሃምሳ ያህሉ እንግሊዛዊው ጄኔራል ማይክል ዳየር በሰጣቸው ትዕዛዝ መሠረት መተኮስ ጀመሩ። ሆኖም አንዳንድ ወታደሮች በመጀመሪያ ወደሰማይ ሲተኩሱ የተመለከተው ጄኔራል «ወደህዝቡ ተኩሱ ፤ ወደዚህ የመጣችሁት ለምን እንደሆነ አታውቁምን?» በማለት በሰጠው ጥብቅ ትዕዛዝ ወታደሮቹ ጭነውት የመጡት 1650 ዙር ጥይት እስኪያልቅ ድረስ ከ 10 - 15 ደቂቃ ያህል ተኮሱ። እያንዳንዱን ሁኔታ ይቆጣጠር የነበረው ጄኔራል ተሰብሳቢዎቹን ለመቅጣት ወስኖ የመጣ ስለነበር «በተለይ ህዝብ በርከት ብሎ ወደተሰበሰበበት ቦታ ላይ እያነጣጠሩ እንዲተኩሱ» ለወታደሮቹ ትዕዛዝ ይሰጥ ነበር። ዕልቂቱን በቤቱ መስኮት ይመለከት የነበረ የዓይን ምስክር በኋላ ለተቋቋመው አጣሪ ኮሚሽን በሰጠው ቃል እንዲህ ብሏል -

> «ከሁሉ የሚያሳዝነው ድርጊት ተኩሱ ያነጣጥር የነበረው ብዙ ህዝብ ሊወጣ ይጋፋበት ወደነበሩት የመውጫ በሮች መሆኑ ነው። በቦታው ሶስት ወይም አራት ጠባብ መውጫዎች የነበሩ ሲሆን ወደነዚህ ሕዝብ ይራወጥ ወደነበረባቸው በሮች ነበር የጥይት ዝናብ የወረደው . . . በዚህ ወከባና ጭንቅንቅ መካከል ብዙዎች በእግር ተረጋግጠው ህይወታቸው አልፏል . . . መሬት ላይ ተዘርረው የነበሩት ላይ እንኳን ጥይት ይተኮስባቸው ነበር።»

ከዕልቂቱ በኋላ በኦፊሴል ወደ 400 ሰዎች ሞተዋል የሚል መረጃ የተሰጠ ቢሆንም በከተማዋ የሚገኙ የመንግሥት ክፍሎች ፣ በሕዝብ የተደረገ ማጣሪያ እንዲሁም ሌሎች መንግሥታዊ አካላት እና የሕክምና ባለሙያዎች የሚኞች ቁጥር ከ 1000 በላይ እንደሚሆን በማስረጃ ይናገራሉ። ሆኖም ግን ይህንን ሁሉ ግፍ እና አሰቃቂ ዕልቂት በመፈጸም ያልረካው ጄኔራልና የላሆር ግዛት ኮሚሽነር የዛቻና የማስፈራሪያ ማስጠንቀቂያዎች በተደጋጋሚ ለህዝቡ የሰጡ ሲሆን በተለይ ጄኔራል ዳየር በዕልቂቱ ማግስት የሚከተለውን ዕብሪት የተሞላበት መመሪያ ለአምሪትሳር ነዋሪዎች አስተላለፈ፡-

> «እናንተ ሰዎች እኔ ወታደር እንደሆን በቅጥ የምትረዱ ይመስለኛል። ሰላም ነው የምትፈልጉት ወይስ ጦርነት? ጦርነትን ከፈለጋችሁ መንግሥት ለዚያ የተዘጋጀ መሆኑን ላሳስባችሁ እወዳለሁ ፤ ሰላምን የምትሹ ከሆነ ደግሞ ትዕዛዜን ተቀበሉና የዘጋችኋቸውን ሱቆች በሙሉ ክፈቱ። ለእኔ እንደሆነ የፈረንሳይ የጦር አውድማዎችም ሆኑ አምሪትሳር አንድ ናቸው። ወታደር ነኝ ፤ ወደፊት ነው የምሄደው ፤ ወደግራ ወይም ወደ ቀኝ አልልም። . . . ስለዚህ ትዕዛዜን ስሙና ሱቆቹን በሙሉ ክፈቱ ፤ እምቢ የምትሉ ከሆነ ደግሞ ሱቆቹ በኃይልና በጠብመንጃ እንዲከፈቱ ይደረጋል። የማይታዘዙትን ሰዎች ሪፖርት በሙሉ አምጡልኝ - ግምባራቸውን ነው የምለው። . . . »

---

[4] እዚህ ላይ ህንዳውያኑ በእንዲህ ዓይነት ስብሰባ ላይ የአገራቸውን ጉዳይ አንስተው መወያየታቸው አይቀሬ እንደሚሆን አንባቢ ልብ ሊል ይገባል። ምክንያቱም በሰላማዊ ትግል የአገር ጉዳይ በማንኛውም አጋጣሚ - በዕድር ፣ ዕቁብ ፣ ለቅሶ ፣ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓል ፣ ወዘተ - ሁለት ሰውና ከዚያ በላይ በሚገኝበት ሥፍራ ሁሉ ውይይት ይደረጋል እንጂ አዳራሽ እስኪከራዩ ወይም ፈቃድ እስኪያገኙ መጠበቅ እንደማያስፈልግ አንባቢው ያስተውሏል።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

እንደዚህ ዓይነቱን የዕብሪት ተግባር መፈጸም ያላቋረጠው ጄኔራል በመቀጠልም በዚያች እንግሊዛዊት የትምህርት ቤት ኃላፊ ላይ ጥቃት የተፈጸመበትን ቦታ «የተቀደሰ» ነው በማለት ማንም በዚያ ማለፍ የሚፈልግ ሰው ሁሉ በሆዱ ተኝቶ እየተሳበ እንዲሄድ ትዕዛዝ አውጥቶ ነበር:: ይህ ሁሉ ግፍና መከራ በሚደርስባቸው ጊዜ ከመንግሥትም (ከእንግሊዛውያን አስተዳዳሪዎችም) ሆነ ከህግ አስከባሪ አካላት መካከል ከህንዳውያኑ ጋር የቆመ አልነበረም:: የጄኔራል ዳየርን አሰቃቂ የግፍ ተግባራት እንዲመረምር የተቋቋመው አጣሪ ኮምሺን ያወጣው ሪፖርትም « . . . ጄኔራሉ ታላቅ ስህተት» መፈጸሙን ከማተትና ድርጊቱም «ሊኮነን የሚገባው ነው» ከማለት አላለፈም:: በተበየነው ውሳኔውም ጄኔራሉ ከሥራ እንዲነሳና ተመልሶ እንዳይቀጠር ብቻ መደረጉ በህንድና በእንግሊዝ አገር የሚገኙ ባለሥልጣናት (የእንግሊዝ ፓርላማ የላዕላይ አካል (House of Lords) ጨምሮ) የጄኔራሉን ድርጊት ምን ያህል ይደግፉ እንደነበር የሚያሳይ ጉልህ ማስረጃ ነው:: (እዚህ ላይ የጄኔራሉን ድርጊት ያወገዙ ባለሥልጣናት መኖራቸውን አለመዘንጋታችን ልብ ይሏል::) ከዚህም ባሻገር ጄኔራሉ ወደ እንግሊዝ አገር ሲመለስ በወቅቱ ይታተም የነበረውና በኋላም ከ *Daily Telegraph* ጋር የተቀላቀለው *Morning Post* የተሰኘው ጋዜጣ ባደረገው የገንዘብ መዋጮ 18,000 የእንግሊዝ ፓውንድ (አንዳንዶች ቁጥሩን እስከ 26,000 ያደርሱታል) እንደ ሽልማት የሰጠው ሲሆን በሴቶች የተሰባሰበ ኮሚቴ ደግሞ «የክብር ጎራዴ» አበርክተውለታል::

በጋንዲ የሰላማዊ ትግል ወቅት ህንዶች አያሌ መከራዎችንና የሰው ልጅ ሊሸከማቸው ይችላል ተብሎ የማይገመቱ ስቃዮችን ተቀብለዋል:: በዚህ የትግል አካሄድ የተነደፈው ማርቲን ሉተር ኪንግ የጋንዲን ተምሳሌት በመውሰድ በአሜሪካ በተካሄደው የጥቁሮችን የሲቪል መብቶች ለማስከበር ያደረገው ተጋድሎ ለኖቤል የሰላም ተሸላሚነት ያበቃው ከመሆን አልፎ የትግሉን ታላቅነትና ተግባራዊነት ያረጋገጠ ለዘመናት ሲታወስ የሚኖር ህያው ምስክር ነው:: በእነዚህ የትግል ዘመናት ዶ/ር ኪንግና የትግል አጋሮቹ በጭካኔና በዘር ጥላቻ የተሞሉትን ሁሉ በየጊዜው ስህተታቸውን በማጋለጥ መብታቸውን ለማስከበር በሚታገሉበት ጊዜ በጥይት ተደብድበዋል ፣ ቤታቸው ተቃጥሏል ፣ የማምለኪያ ቦታዎቻቸው በቦምብ ጋይተዋል ፣ የአልሞ ተኳሾች ሰለባ ሆነዋል ፣ በፖሊስ ውሻዎች ኢሰብኣዊ ጥቃት ደርሶባቸዋል ፣ ከመንግሥት ሹማምንትና ከህግ አስከባሪዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በተቀነባበረ ሴራ ጥቃት ደርሶባቸዋል:: ይህንን ሁሉ ግን በትዕግስት ተወጥተዋል:: የትግሉን እልህ አስጨራሽነትና ተስፋ አስቆራጭነት ተገንዝበው ከጅምሩ ራሳቸውን ለዚያ አዘጋጅተው የገቡ እስከመጨረሻው በመጽናት ካሰቡበት የደረሱ ቢሆንም በየጊዜው ይደርስባቸው በነበረው ጥቃት የተማረሩ «እስከመቼ» በማለት «ስማ ሠራዊት ፣ ምታ ነጋሪት» ማለታቸውም አልቀረም:: (እዚህ ላይ ታዋቂውን የተማሪዎች የሰላማዊ ትግል አስተባባሪ ኮሚቴ (SNCC) መሪ የነበረውን Stokely Carmichael በኋላ Kwame Ture ተብሎ የተጠራውን ለዓብነት ይጠቅሷል::)

ማኅትማ ጋንዲ ህይወቱ በሂንዱ እምነት ጽንፈኛ ወጣት ካለፈች በኋላ በህይወት በነበረ ጊዜ በሰጠው ኑዛዜ መሠረት የተወሰነው አመዱ በዓለማችን ባሉ ታላላቅ ወንዞች (ናይል ፣ ቴምስ ፣ ቮልጋ ወዘተ) እንዲፈስ መደረጉ ይሆን ዶ/ር ኪንግን ጨምሮ የበርማዋ አን ሳን ሱ ኪ በቅርብ ጊዜ ደግሞ ባገራችን የተጀመረው የፖለቲካ እንቅስቃሴ መሪዎች በዚህ የሰላማዊ ትግል እየተለከፉ የመጡት?

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

## አን ሳን ሱ ኪ በበርማ

የቡድሃ እምነት ጥብቅ ተከታይ የሆነችውና በጋንዲ የሰላማዊ ትግል ፍጹም አማኝ የሆነችው አን ሳን ሱ ኪ የመጀመሪያዋን ዲግሪ ከኦክስፎርድ ፣ የዶክትሬት ዲግሪዋን[5] ደግሞ ከሎንዶን ዩኒቨርሲቲ የተቀበለች ሲሆን ከእንግሊዛዊው ባሏ ሁለት ወንድ ልጆችን ወልዳለች:: በአገሯ በርማ በ August 8, 1988 በተደረገው ህዝባዊ አመጽ (በተለምዶ የ8-8-88 ዓመጽ[6] ተብሎ የሚጠራው) ተማሪዎች ባስነሱት ተቃውሞ ወታደራዊው አምባገነን መንግሥት ተቃውሞውን በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ በርማውያንን በመግደል ባስቆመበት ጊዜ ነበር አን ሳን ሱ ኪ የተቃዋሚ ፓርቲ ተምሳሌት ሆና ብቅ ያለችው:: (በወቅቱ የተገደሉት በርማውያንና የቡድሃ እምነት መነኮሳት ቁጥር በውል የማይታወቅ ሲሆን ከ 3,000 የማያንሱ እንደተጨፈጨፉ ብዙዎች ይገምታሉ::) ከዚህ የግፍ እርምጃ በኋላ ነበር አን ሳን ሱ ኪ «ብሔራዊ የዴሞክራሲ ሊግ» የተሰኘ ፓርቲ መሥርታ በአገሯ ዴሞክራሲ ለማምጣት መታገል የጀመረችው:: ሆኖም ብዙ ሳይቆይ ወታደራዊው አምባገነን መንግሥት የቁም እስረኛ ያደረጋት ሲሆን ነጻነቷን ለማግኘት የምትፈልግ ከሆነ አገሯን ለቅቃ መሄድ እንደምትችል ከመንግሥት ይነገራታል:: ከአገሬ ወጥቼ ነጻነትም ትግልም የለም ያለችው አን ሳን ሱ ኪ የቀረበላትን ጥሪ ፈጽሞ እንደማትቀበል በግልጽ አስታወቀች::

ይህ ከሆነ ከሁለት ዓመታት በኋላ ወታደራዊው አምባገነን መንግሥት በጠራው አጠቃላይ ምርጫ የአን ሳን ሱ ኪ ፓርቲ «ብሔራዊ የዴሞክራሲ ሊግ» ወሳኝ ድል የተጎናጸፈ በመሆኑ ዶ/ር ሱ ኪ የጠቅላይ ሚኒስትርነትን ሥልጣን መረከብ ሲኖርባት ሽንፈትን መቀበል እንደ እሬት የመረረው ወታደራዊ ጁንታ አሻፈረኝ በማለቱ መሪዋን ሱ ኪን እንደገና ወደ ቁም እስር በመላክና ዓለም አቀፋዊ ውግዘትን በመናቅ ሥልጣኑን ለማንም አላስነካም በማለት ፍጹም አምባገነናዊነቱን አረጋገጠ:: አፈናው እየቀጠለ በመሄዱም አን ሳን ሱ ኪ በተለያየ ጊዜ የተሰጣትን ሽልማቶች (የኖቤል የሰላም ሽልማትንም ጨምሮ) በአካል ተገኝታ ለመቀበል አልቻለችም ፤ ምክንያቱም አንድ ጊዜ ከአገር ከወጣች የመመለሻ ፈቃድ እንደማታገኝ ከመንግሥት በግልጽ ተነግሯታልና:: እንግሊዛዊው ባለቤቷ በካንሰር ሲሰቃይ ቆይቶ ለሞት አፋፍ በተቃረበበት ወቅት እንኳን ቤተሰቧን ወደዚያው ሄዳ ለማየት እንድትችል (ሁለቱ ወንድ ልጆቿ ከአባታቸው ጋር እዚያው እንግሊዝ አገር ናቸው) ፈቃድ ብትጠይቅም አምባገነኑ ወታደራዊ መንግሥት አንዴ ከወጣች የመመለሻ ፈቃድ እንደማታገኝ ማስጠንቀቂያ የሰጣት በመሆኑ የህይወት ጓደኛዋን ሳታየው ወደመቃብር ወረደ - ልጆቿንም እስካሁን ለረጅም ዓመታት ተለይታቸው ትገኛለች:: እዚህ ላይ ለወላጅ እናት ይህ ምን ያህል ከባድ ሽክም መሆኑን መገመት አያዳግትም::

አን ሳን ሱ ኪ ከፓርቲዋ ኃላፊዎችና ደጋፊዎች እንዲሁም ከዓለም አቀፍ ጎብኚዎች እንዳትገናኝ ጥብቅ እቀባ የተደረገባት ቢሆንም ከዓመታት በኋላ ከተባበሩት መንግሥታት ከፍተኛ ባለሥልጣናት ጋር እንድትገናኝ በተፈቀደላት መሠረት ባለፈው ዓመት የቡድሃ መነኮሳት በአገራቸው የተንሰራፋውን ግፍና ጭቆና ተያይዞ የመጣውን የኑሮ ውድነት በመቃወም ሰልፍ በወጡ ጊዜ በመንግሥት አፈና ከተደረገባቸውና ከተገደሉ በኋላ በቅርቡ የተባበሩት መንግሥታት ረዳት ዋና ጸሃፊ ኢብራሒም ጋምባሪ እንዲነጋግሯት በመደረጉ ከሦስት ዓመታት በኋላ ከፓርቲዋ ኃላፊዎች ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ መገናኘት ችላለች:: ሆኖም የበርማ ወታደራዊ አምባገነን ከተባበሩት መንግሥታትም ሆነ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች በተደጋጋሚ የቀረበለትን የዕርቅና የብሔራዊ መንግሥት ምስረታ ሃሳብ ሲቃወም የቆየ ሲሆን በቅርቡም ይባስ ብሎ አን ሳን ሱ ኪ የተሰጣትን የኖቤል ሽልማት ገንዘብ «ግብር ሳትከፍል ወይም በአገር ውስጥ ሳትጠቀምበት ከቤተሰብዋ ጋር

---

[5] http://www.npr.org/templates/story/story.php?storyId=14865943
[6] http://en.wikipedia.org/wiki/8888_Uprising

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

በመነጋገር ከአገር ውጪ አባክናዋለች»[7] በማለት ክስ መመስረቱን ያስታወቀ ሲሆን «እስካሁን ድረስ ለሰራችው ጥፋት ተገቢው ቅጣት ይበየንባት ቢባል ኖሮ እድሜልኳን እስርቤት ትማቅቅ እንደነበር» የተናገረው የመንግሥት መግለጫ ሲቀጥል መንግሥት ግን «ርኅሩኅ ስለሆነ ከእስርቤት ይልቅ አሁን ባለችበት ሁኔታ እንድትቆይ» ማድረጉን ተናግሯል:: ይህንን መግለጫ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶችና የተባበሩት መንግሥታት «ቀልድ» በማለት ያጣጣሉት ሲሆን አን ሳን ሱ ኪ ያለችበት ሁኔታ ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ ማድረግ የማትችልበትና ቁም የታሰረችበትም ቤት በወታደሮች ጥብቅ ቁጥጥር የሚደረግበት ከመሆኑ ባሻገር ካለ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣን ፈቃድ ከማንም ጋር መገናኘት የማትችልና መብቷ በፍጹም የተገፈፈ የዴሞክራሲ ታጋይ መሆኗን በድጋሚ አስታውሰዋል:: ይህንን ሁሉ ግፍና መከራ እንዲሁም ከቤተሰብዋ ለሁለት አስርተ ዓመታት የመለየትን ስቃይ እስካሁን እየተቀበለች ያለችው ይህች የበርማ የዴሞክራሲ ፋና ወጊ ከፍርሃት ነጻ መውጣት ስላለባቸው የአገሯ አምባገነኖችና የሥርዓቱ ፍርፋሪ ለቃሚዎች **"Freedom From Fear"**[8] በተሰኘው ታዋቂ ንግግሯ በድፍረት እንዲህ ብላቸዋለች:-

> **"It is not power that corrupts but fear. Fear of losing power corrupts those who wield it and fear of the scourge of power corrupts those who are subject to it."**

ለደጋፊዎቿና ለዴሞክራሲ አፍቃሪዎች በሙሉ ደግሞ ይህንን መልዕክት በዚያው ንግግሯ ስጥታቸው ነበር:-

> **"Saints, it has been said, are the sinners who go on trying. So free men are the oppressed who go on trying and who in the process make themselves fit to bear the responsibilities and to uphold the disciplines which will maintain a free society. Among the basic freedoms to which men aspire that their lives might be full and uncramped, freedom from fear stands out as both a means and an end. A people who would build a nation in which strong, democratic institutions are firmly established as a guarantee against state-induced power must first learn to liberate their own minds from apathy and fear."**

## በአገራችን ለሚካሄደው ሰላማዊ ትግል በውጪ ያለው ኢትዮጵያዊ ሚና

እጅግ ጥልቅና ብዙ ሊባልበት ስለሚችለው የሰላማዊ ትግል በመጠኑ ይህንን ያህል ካልኩ አሁን ደግሞ ከላይ በጽሑፌ መግቢያ ላይ ወዳነሳሁት ሃሳብ ልመለስ::

ወደኋላ መለስ ብለን የአገራችንን የቅርብም ሆነ የሩቅ ታሪክ በምንዳስስበት ጊዜ ኢትዮጵያዊነት ከነፍጥ ማንሳት ተለይቶ የነበረበትን ዘመን ማግኘት አዳጋች ነው:: ሰላማችንን ፣ ድላችንን ፣ ወዘተ ስናገኝና ስናጣ የኖርነው በነፍጥ ነው:: ታዲያ ከዚህ አኳያ ከተመለከትነው ሰላማዊ ትግል ለአገራችን የፖለቲካ አካሄድ ባዕድ ሊመስል ይችላል:: ለዚህም ሊሆን ይችላል አንዳንዶቻችን «ነጻነትን ለመጎናጸፍ ሰላማዊ መንገድ መከተል?» በማለት የማያቋርጥ ጥያቄ የምንጠይቀው ፤ ምናልባትም ለሌሎቻችን ይህ የፖለቲካ መስመር «የቅንጦት መንገድ» የሚመስለን - ማለት ሁኔታዎች ሲመቹ የምንከተለው የፖለቲካ አካሄድ ዓይነት:: ሆኖም እውነታው ይህ ሳይሆን ሰላማዊ የትግል መንገድ ተፈትኖ የነጠረ እና ለአንድ ኅብረተሰብ በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ላሉ

---

[7] http://www.nytimes.com/2007/01/19/world/asia/19myanmar.html?_r=1&oref=slogin
[8] http://www.dassk.com/contents.php?id=416

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የማያቋርጥ የጦርነት ታሪክ ላዳበሩ አገራት አቻ የማይገኝለት የትግል መንገድ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም::

ከዚህ ዓይነት አስተሳሰብ በመነሳትም ይሆናል ባገራችን የተለየ ፖለቲካ አካሄድ የዛሬ ሦስት ዓመት አካባቢ ሲያቆጠቁጥ የተመለከትነው:: በዚህ ወቅት የተነሳው የፖለቲካ እንቅስቅሴ ሥልጣንን የሙጥኝ ያለውን መንግሥት በምርጫ ድል መንሳት እንደሚችል ባገኘው ጠባብ ቀዳዳ ሰንጥቆ በመግባት መላ የኢትዮጵያን ሕዝብ ድጋፍ ለማግኘት በቃ:: በመሠረቱ ሰላማዊ ትግል ነገሮች ሲደሉ እና ሁኔታዎች ሲመቻቹ የምናደርገው ትግል እንዳልሆነ ይህ በራሱ በቂ ማስረጃ ሊሆን ይችላል:: በነፍጥ የሥልጣን ኮርቻ ላይ የተደላደለው አካልም በምርጫ ወረቀት መውረድ ሊዋጥለት የማይቻል ሃቅ ሆነበት:: ትግሉንም ለማፈን ሲል የሚችለውን ገደለ ፤ የተቀረውንም እስር ቤት አጎረ:: ቀጥሎም የዴሞክራሲያዊ ተቋማት ግንባታ ጥያቄም ይሁን ባጠቃላይ የፍትሕ ፣ የነጻነት ፣ የሰላም ፣ የዕርቅ ወዘተ ጥያቄዎችን በለመደው በነፍጥ ነው ምላሽ ማግኘት ያለባቸው አለ:: አደረገውም ፤ እያደረገውም ይገኛል::

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ሰላማዊ ትግል አማራጭ ሲኖር የሚጀምር አማራጩ ሲዘጋ ደግሞ የሚቆም ትግል አይደለም:: ሰላማዊ ትግል በምርጫ ተሳትፎ ተጀምሮ በሰላማዊ ሰልፍ የሚያበቃ ትግልም አይደለም:: ቢሆንማ ኖሮ እነ ጋንዲ ከ50 ዓመት በላይ እነ ማርቲን ሉተር ኪንግ ከ15 ዓመት በላይ አን ሳን ሱ ኪ ደግሞ ሁለት አስርተ ዓመታት ባልወሰደባቸው ነበር:: ይህም እንኳን ሆኖ እስካሁን ትግሉ አላቆመም:: ምክንያቱም ከዚህ በፊት ለመግለጽ እንደተሞከረው የሰላማዊ ትግል ከራስ የሚጀምር በመሆኑና ከዚያም ሲቀጥል ዶ/ር ኪንግ እንዳለው «. . . እሴት ብለን በያዝናቸው ነገሮች ላይ ሥር ነቀል ለውጥ ማምጣትን»[9] የሚጠይቅ በመሆኑ ነው:: ሰላማዊ የትግል መንገድ አሩን ጋንዲ (የማሃትማ ጋንዲ የልጅ ልጅ ነው) እንዳለው « . . . ጦርነትን ፣ ሽብርን ፣ ውጊያን ፣ . . . አለመጠቀም ብቻ ሳይሆን . . . ጥላቻን ፣ ሰዎችን በጅምላ መወንጀልን ፣ በሰዎች ላይ ስም መለጠፍን ፣ . . . የመሳሰሉትን እና መልካም የሚመስሉ ነገር ግን ሰዎችን ከሚጎዱ ነገሮች በሙሉ መታቀብንም ይጨምራል::»[10] ይህንን ሃሳብ የትግሉ አራማጆችም ሆኑ በተለይ ደግሞ ተከታዮችና ደጋፊዎች በአንክሮ ሊያጤኑት የሚገባ ነው:: ይህንን በማድረግም ሂደት ውስጥ ነው ሰላማዊ ትግል በሚያገኘው ቀጭን ቀዳዳ ሁሉ ሰንጥቆ በመግባት እና በተጠበቀም ሆነ ባልተጠበቀ አጋጣሚ ዓላማውን ለማሳካት የሚጥረው:: የሰላማዊ ትግል ሕዝብን ያስተምራል ፤ ሕዝብን በዕውቀት ያስታጥቃል ፣ በሚያገኘው አጋጣሚ ተጠቅሞም ሕዝብን የሥልጣን ባለቤት ያደርጋል:: በአገራችን በምርጫ ወቅት የተደረገውም ከዚህ ጋር ተዛማጅነት ያለው ነው እንጂ ፤ ነገሮች ስለተሟሉ እና ሁኔታዎች ስለተደላደሉ «እስቲ እንታግል» ተብሎ በድሎት የተጀመረ ትግል አልነበረም:: ቢሆንማ ኖሮ ከታጋዮቹ ይልቅ ፈቃጁን ባለውለታ ማድረግ በተገባ ነበር:: ፈቃጁማ ለመሪዎቻችን የሰጠው «የትግል አማራጭ» «ወይ ጫካ ግቡ ፤ ወይ አገር ለቅቃችሁ ሂዱ ካልሆነም አርፋችሁ ቁጭ በሉ» የሚል እንደነበር ዶ/ር ብርሃኑ መናገራቸውን አስታውሳለሁ:: የሕዝባችን እና የመሪዎቻችን መልስ ግን «መልሱ አልተሰጠም» በማለት ከሦስቱ ምርጫዎች ውጪ «አገር ውስጥ በመሆን የሰላማዊ ትግል መቀጠል» ብለው በመወሰናቸው ነበር ቃሊቲ የወረዱት::

ስለዚህ ከዚህ በላይ ስለ ሰላማዊ ትግል ምንነት በተለያ ክፍሎች ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች እና ሌሎች አገሮች እያካሄዱ ካሉት የትግል ተሞክሮ አኳያ ስንመለከተው ሰላማዊ ትግል በአገራችን ገና ተጀመረ ነው ማለት የምንችለው:: ገና ብዙ አስተሳሰቦች እና ለዘመናት ታቅፈናቸው ከቆየናቸው አመለካከቶች ነጻ መውጣት አለብን:: ነጻነትን ፣ ፍትሕን ፣ ዴሞክራሲን መናፈቅ ብቻ ሳይሆን እነዚህን ድሎች በምንጎናጸፍበት ጊዜ በተገቢው ለመንከባከብና በተግባር በሥራ ላይ ለማዋል የተዘጋጀን መሆን አለብን:: የዚህን እልህ

---

[9] http://greensborominimumwage.blogspot.com/2007/07/martin-luther-king-jr-fierce-urgency-of.html

[10] Nagler, M. The Search for a Nonviolent Future. p. x

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

አስጨራሽ የትግል መስመር ሊወስድ የሚችለውን ጊዜ በመመልከትም ሊሆን ይችላል አንዳንዶች ድሉ የዘገየ የሚመስላቸው:: ሆኖም ግን ነጻነት/ድል አይዘገይም ፤ አይፈጥንም:: ወቅቱን ጠብቆና የሕዝባችን እና የመሪዎቻችን የመንፈስ ፣ የሞራል እና የስነ ልቡና ዝግጅት አስተማማኝ ደረጃ ላይ በሚደርስበት ወቅትና ለዘመናት የናፈቀውን ነጻነት ሕዝባችን ባግባቡ በሥራ ላይ ለማዋልና ወደፊትም ለመንከባከብ ዝግጁ በሚሆንበት ጊዜ ነጻነት እውን ይሆናል:: ታዲያ በዚህ ዝግጅት ማብቂያ ላይ የሚነሳውን ኃይል ማንም ሊገድበውም ሆነ ሊከላከለው እንዲሁም ሊያስቆመው አይችልም::

ይህ ከሆነ ዘንዳ ለዚህ እንዴት ነው የምንዘጋጀው? ይህንን በአገራችን ገና በማቆጥቆጥ ላይ የሚገኘውን የትግል መስመርስ እንዴት ነው እንዲቀጥል ማድረግ የምንችለው? ለሚሉና ለመሳሰሉ ጥያቄዎች የሚከተሉትን ሃሳቦች ለማቅረብ እፈልጋለሁ:: በቅድሚያ ግን ወደዝርዝር ሃሳቦቹ ከመግባቴ በፊት እኔ ከሩቅ ሆኜ አገር ቤት መደረግ ያለበትን የትግል ሁኔታ እንዴት መሆን እንዳለበት ለመናገር ይከብደኛል የሚለውን የአቶ አንዳርጋቸውን ሃሳብ በሙሉ የምጋራ መሆኔን እየገለጽኩ ፤ ትግሉ እዚያው አገር ቤት እንደሆነና ይህ የትግል አካሄድ እልህ አስጨራሽ መሆኑን ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በደንብ ልናስተውለው በምንችል መልኩ በመጽሐፋቸው እና በንግግራቸው ያስገነዘቡንን በማስታወስም ነው:: ስለዚህ ከዚህ በታች የተጠቀሱት የመፍትሔ ጠቋሚ ነጥቦች በአገር ቤት ያለው ትግል በምን መልኩ መካሄድ እንዳለበት የሚዘረዝር ሳይሆን እኛ በውጪ ያለነው በአገር ውስጥ ያለውን የትግል እንቅስቃሴ እንዴት መርዳት እንችላለን ለሚለው ጥቂት ነጥቦችን ለመጠቆም ነው:: በአገር ቤት ያለው ትግል እጅግ ተለዋዋጭ ፣ በጣም ፈጣን ውሳኔዎችን የሚጠይቅ እና በተገኘው አጋጣሚ ሰንጥቆ የመግባትን ሁኔታ የሚሻ በመሆኑ እዚህ በርቀት ሆኜ በሰማይ ላይ ያሉትን ከዋክብት እንደሚመረምር የስነ ከዋክብት ሊቅ በየቀኑ ጨካኙን እና የፈለገውን ነገር በፈለገው ሰዓትና ጊዜ ለማድረግ ቅንጣት የማይከብደውን የማፊያ ቡድን በእያንዳንዷ ደቂቃ እየተጋፈጡ ላሉት የሰላም አርበኞች ሊከተሉት የሚገባቸውን መንገዶችን ልነግራቸውም ሆነ የመፍትሔ ሃሳብ ልጠቁማቸው የሞራል ብቃቱ ስለሌለኝ ነው:: በዚህ ባለሁበት አገር እኔን መሳይ ኢትዮጵያውያን በምን መልኩ የአገርቤቱን ትግል መርዳት እንችላለን ለሚለው ጥያቄ ግን የሚከተሉትን ነጥቦች ለመጠቆም እፈልጋለሁ::

1. ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የሰላማዊ ትግል ከራስ የሚጀምርና የብዙሃንን ህብረት የሚጠይቅ በመሆኑ ሁላችንም በመካከላችን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተከሰተውን መከፋፈል ፍጹም ወደኋላ በማለት በአንድነት ለጋራ ዓላማ መተባበር አለብን:: ይህ የጋራ ዓላማ «በሕዝቦች ፈቃደኝነት የምትመሠረተው አዲሲቱ ኢትዮጵያ» መሆኑን ሁላችንም የምናምንበት እስከሆነ ድረስ ሊያስማማን በሚችለው ነገር ላይ ሁልጊዜ እየተነጋገርን እና ያንን ሃሳብ እያዳበርን መሄድ ይገባናል እንጂ በሚለያዩን ጥቃቅን ነገሮች አላስፈላጊ ጊዜ በመውሰድ መነታረኩ «ስንከፋፈል እንወድቃለን» የሚለውን አባባል ትክክለኛ ነት ከማረጋገጥ አልፎ በዋንኛነት የሚጠቅመው እንድንከፋፈል መንገዱን የጠረገልንን ነው:: ስለዚህ ሁላችንም - የመገናኛ ብዙሃን ፣ አፍቃሪ ዴሞክራሲ የሆኑ ድረ ገጾች ፣ የፓልቶክ ክፍሎች ፣ ወዘተ - ስብሰባ ተጠርቶ አዳራሹ በባዶ ወንበር ስለመሙላቱ ወይም ትግሉን ሊቀለብሱ እነ እገሌ እያሴሩ ነው ወዘተ በማለት በየደቂቃውና ሰዓቱ ከመዘገብና ከመወያየት ይልቅ በአካሄድ ላይ ያለን ልዩነት እንዳለ ሆኖ ግቡን እውን ለማድረግ ሊያስተሳስረን ወደሚችል የአንድነት ሃሳብ ብናተኩር ጥንካሬአችን እየጎለበተ ይሄዳል:: እዚህ ላይ «ህዝብ መረጃን የማወቅ መብቱን» ለመቃወም ሳይሆን እስካሁን ድረስ ከበቂ በላይ አውቀናልና እስቲ ሃሳባችንን ሆነ ብርታታችንን ሊያጠናክረን ወደሚችል ሃሳብ ይበልጥ እናተኩር ለማለት ነው:: ከዚህ አኳያ አቶ ተፈሪ መንግሥቴ[11] በቅርቡ **H.R. 2003: A Cause that Unifies the**

---

[11] http://ethioforum.org/wp/?p=30

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

**Fragmented Diaspora!** በሚል ርዕስ ባወጡት ጽሑፍ ላይ በግልጽ እንዳስረዱት በተለያየ የፖለቲካ አካሄድ ተከፋፍለን ያለነው ሁሉ ሃሳባችን ሁላችንም ልንስማማበት ወደሚችል እንደ **H.R. 2003** ዓይነት የተቀደሱ ጉዳዮች ላይ በማተኮር ይበልጥ አንድነታችንን እናጠናክር። ከጥቂት ወራቶች በፊት **Jena, Louisiana**[12] በጥቁርና በነጭ ተማሪዎች መካከል የተፈጠረ አለመግባባት ወደ ዘር ፖለቲካ ተሸጋግሮ በነበረበት ወቅት ለነጮቹ ተማሪዎች የወገነ ኢፍትሐዊ ውሳኔ መሰጠቱን የተቃወሙ ጥቁር አሜሪካውያን አለአግባብ የተሰጠውን ፍርድ በመቃወም ከአጠቃላይ የአሜሪካ ግዛቶች ተቃዎሞአቸውን ለመግለጽ ወደዚህች ትንሽ ከተማ እንደተመሙ ሁሉ እኛም የአገራችንን ጉዳይ በተመለከተ በአንድነት በምንጠራበት ቦታ ሁሉ በመገኘት ሕብረታችንን እና ለአገራችን ያለንን ጥልቅ ስሜት በማሳየት አንድነታችንን በምናገኘው አጋጣሚ ሁሉ መግለጽና ለተመሳሳይ ተግባራት ይበልጥ በአንድነት ለመስራት ቁርጠኛ አቋም መውሰድ ይኖርብናል።

2. ከዚህ በፊት በታሪክ የተካሄዱትን የሰላማዊ ትግሎችን በምንመለከትበት ጊዜ የትግሉ መሪዎች ከሃይማኖት ጋር የጠበቀ ትስስር እንዳላቸው ለመረዳት እንችላለን። በተለይ ማርቲን ሉተር ኪንግ በስነ መለኮት የዶክትሬት ዲግሪ የነበረው ሲሆን የባፕቲስት ቤ/ክ ፓስተርም (ካህን) ነበር። በትግሉ ወቅት በርካታዎቹን ንግግሮች ያደረገው ከመጽሐፍ ቅዱስ በመጥቀስ በቤ/ክ ውስጥ ለተሰበሰቡ ምዕመናን ነበር። በመሠረቱ የፍትሕ እና የሰብዓዊ መብት ጥያቄዎች የፖለቲካ ጥያቄች ሳይሆኑ ፈጣሪያችን እኛ እንድንለማመዳቸው የሚጠብቅብን ለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ሲጠቅስ «ሰው ሆይ እግዚአብሔር ከአንተ ዘንድ የሚሻው ምንድር ነው? ፍርድን ታደርግ ዘንድ ፤ ምሕረትን ትወድድ ዘንድ ፤ . . . አይደለምን?» ይላል።[13] (ሚክ. 6:8) ወዳገራችን ታሪክ ስንመለስ ደግሞ ጀግናውን አቡነ ጴጥሮስን እናገኛለን። ጣሊያን አገራችንን ወርሮ ሕዝቡ ሰጥ ለጥ ብሎ እንዲገዛለት አቡኑን ለመጠቀም ቢሞክርም «እንኳን ሕዝቡ ምድሪቱ ላንተ ብትገዛ ውጉዝ ትሁን» በማለት ለነጻነት መቆም የሃይማኖት ግዴታቸው መሆኑን የህይወት መስዋዕትነት በመክፈል የመሰከሩ ናቸው። አሁን ያለው ትግል በውጪ ያለነውን ይህንን ያህል መስዋዕትነት እንድንከፍል የሚጠይቅ ባይሆንም የሃይማኖት መሪዎችም ሆኑ የማንኛውም እምነት ተከታዮች ለነጻነትና ለፍትሕ በሚደረገው የሰላማዊ ትግል ውስጥ ከጸሎት የበለጠ የተሳትፎ ድጋፋቸውን መለገስ እንደሚገባቸው ከቀደምት የሃይማኖት መሪዎች ትምህርት በመውሰድ በትግሉ ውስጥ መሳተፍ መጀመር አለባቸው። በዚህ አጋጣሚ ይህ ጥሪ ለሁሉም የሃይማኖት ድርጅቶች የቀረበ ሲሆን ከእንግዲህ ወዲህ የሃይማኖት መስበኪያ ቦታዎች ከእምነቱ ትምህርት ጎን ለጎን «የኢትዮጵያ ትንሣኤ» የሚሰበክበት መሆን አለባቸው። የሁሉም ሃይማኖት ድርጅት መሪዎችም ህዝባችን ነጻነቱን እስኪጎናጸፍ ድረስ በትግሉ ጊዜ ሁሉ ካሁኑ ጀምሮ ከእምነታቸው ትምህርት በተጓዳኝ በኢትዮጵያ በፍትሕ መጓደልና በነጻነት እጦት ውስጥ ለሚገኘው ሕዝባቸው ያላቸውን ድጋፍ በጽናት ማሳየትና ትግሉ በሚጠይቀው መስክ ለመርዳት ምዕመኖቻቸውን ማስተባበር ከዛሬ መጀመር አለባቸው። በኢትዮጵያ ጉዳይ የማያገባው ማንም የለም ፤ አገራችንን ከልብ ከወደድን ሁላችንም እንደዓቅማችን ልንሰራው የምንችል ሥራ አለን። ይህንን ለማድረግ ደግሞ ሃይማኖታችን ምክንያት ወይም እንቅፋት ሊሆን አይችልም።

---

[12] http://abcnews.go.com/US/wireStory?id=3628976

[13] መጽሐፍ ቅዱስ በሌሎች ቦታዎች ላይ የፍትሕንና የቅንነትን ተግባራት ለተጨቆኑና ደጋፊ ለሌላቸው ሁሉ እንድናደርግ የሚያስገነዝብ ሲሆን እነዚህን ተግባራት መፈጸም ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ብቻ የተጠቀሱ ወይም በክርስትና ሃይማኖት ብቻ የሚገኙ ሳይሆኑ ሌሎችም ሃይማኖቶች (ለምሳሌ እስልምና) በተመሳሳይ መልኩ የሚጋሯቸው መሆኑ እሙን ነው።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

3. ከኢትዮጵያ ውጪ በምንኖርበት ጊዜ ባለን የግንኙነት መስመር ሁሉ በመጠቀም ከሌሎች የሰላማዊ ታጋዮች ጋር ዓለም አቀፋዊ ህብረት (solidarity) በመመሥረት በአገራችን እየተካሄደ ያለውን አፈና ፣ የሰብአዊ መብት ረገጣ ፣ አምባገነናዊ አስተዳደር ፣ ወዘተ በምናገኘው አጋጣሚ ሁሉ ትኩረት ሊስብ በሚችል መልኩ ማጋለጣችንን በተጠናከረ መንገድ መቀጠል ሌላው በአንክሮ ልናስብበት የሚገባ ጉዳይ ነው። እዚህ ላይ ሊስተዋል የሚገባው ነገር ትግሉን ዓለም አቀፋዊ ይዘት እንዲኖረው ማድረግ በአገራችን ሕዝብ ላይ የሚደርሰውን ሰቆቃ ከሌሎች ጋር በንጽጽር ለማቅረብ የሚያስችለን ከመሆኑ ባሻገር የውጪ መንግሥታት የሚያደርጉት ድጎማ ለምን ሥራ ላይ እየዋለ እንደሆነ በማያሻማ መልኩ ይፋ ለማድረግ የሚረዳ ዓይነተኛ ዕድል የሚሰጥ በመሆኑም ነው። እንደዚህ ላለው ተግባር አትኩሮት መስጠቱ ምናልባት ለአንዳንዶቻችን «ይህ እኮ የአደባባይ ምስጢር ነው ፤ የውጪ መንግሥታት ባገራችን የሚካሄደውን እያወቁ እኮ ነው ጆሮ ዳባ ያሉት» የሚያስብል ሊሆን ይችላል። ልብ ብለን ከተመለከትነው ግን አሁን በ H.R. 2003 ከምናደርገው ትብብር በስተቀር መሪዎቻችን ከተፈቱ ወዲህ በሕዝባዊ ስብሰባም ሆነ በተቃውሞ ሰልፍ የምናደርጋቸው ተግባራት የተገደቡ ይመስላል። ሆኖ ግን የውጪ መንግሥታት ሹማምንትን እና ሕግ አውጪዎችን ከመወትወት (Lobbying) ጀምሮ ከሌሎች የሰላማዊ ታጋዮች ጋር ኅብረት በመመስረትና ዓለም አቀፋዊ መድረኮችን በማዘጋጀት ትግሉን ማስፋትና የብዙዎችን የትኩረት አቅጣጫ ለመሳብ የሚደረገው ጥረት በተጠናከረ መልኩ ሊካሄድ ይገባዋል።

4. የሰላማዊ ትግል ዋንኛ ተግባሩ ሕዝብን በዕውቀት ማስታጠቅ እና ማበልጸግ (empower) ማድረግ በመሆኑ ዓለማችን አሁን የደረሰችበትን ከፍተኛ የቴክኖሎጂ ዕድገት በመጠቀም ለአገራችን ሕዝብ በቀጥታ በየቀኑ የሚተላለፍ እና የማስተላለፊያ ብቃቱ ደግሞ አስተማማኝ የሆነ የራዲዮ አገልግሎት በቅርቡ መጀመርና ይህንንም ስርጭት በቀን ውስጥ ለተወሰኑ ሰዓታት ማተላለፍ እንዲጀምር በማድረግ በሂደት የረጅም ሰዓታት ፕሮግራሞችን የሚያካሂድ እንዲሆን ዕቅድ መወጠን በመወጠን ለተግባራዊነቱ በህብረት መንቀሳቀስ። ከዚህም በተጨማሪ በተወሰኑ የአገራችን ቦታዎች ሊዳረስ የሚችልና ለተወሰነ ሰዓታት ሊተላለፍ የሚችል የቴሌቪዥን አገልግሎት መጀመር የሚቻልበትን መሠረት በመጣል በውጪ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ በገንዘብ ፣ በዕውቀት ፣ ወዘተ መተባበር የሚችልበትን መንገድ ማመቻቸት[14]። ዓለማችን ካለችበት የቴክኖሎጂ እድገት አኳያ ባሁኑ ጊዜ በየትኛውም የአለም ክፍል የሚካሄደውን ነገር በሙሉ በየደቂቃው የሚዘገብበት (real time reporting) ጥበብ በተደረሰበት ጊዜ እስከመቼ ነው ሕዝባችን የመረጃ ጥማቱን ለማርካት በአሜሪካ ድምጽ እና በጀርመን ድምጽ ሬዲዮኖች ላይ ብቻ እያደረገ የሚኖረው? እስከመቼስ ነው በአንድ ሰዓት የፕሮግራም ዝግጅት ተወስኖ የሚኖረው? ይህንን ዓይነት የመረጃ ቅርርብ ከአገራችን ሕዝብ ጋር እየፈጠርን አቶ አንዳርጋቸው በዚህ ትግል ውስጥ አታጋይ መፈክሮች እንደሚስፈልጉንና ምን መሆን እንዳለባቸው እንደጠቆሙት ሁሉ በአሜሪካ የሲቪል መብቶች ትግል ወቅት ይጠቀሙ እንደነበሩት እንደ "we shall overcome" ዓይነት በሁሉም ቦታ ሊዘመሩ

---

[14] ይህንን የምለው እንደው በስሜት በመነሳሳት ሳይሆን ሌሎች ካደረጉት ልምድ በመነሳት እንደሆነ አንባቢው እንዲገነዘብልኝ እፈልጋለሁ። የኤሌክትሮኒክ ሚዲያው ስርጭት ባጭር ጊዜ ውስጥ በቀጥታ ለማካሄድ የሚያዳግት እንኳን ቢሆን ዘመኑ ባፈራቸው የቴክኖሎጂ አማራጮች በመጠቀም ለሕዝባችን መረጃ እንዲደርሰው የማድረጊያ ብዙ መንገዶች አሉ። የሁኔታዎችን መልክ መያዝ ከተመለከትን በኋላ በነዚህ ጉዳዮች ላይ በዝርዝር መወያየት ይቻላል።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የሚችሉ አታጋይ መዝሙሮችን እኛም በማዘጋጀት በአገራችን ካለው ሕዝብ ጋር በመንፈስ የመገናኛ መስመር እንድንዘረጋ ያስችለናል።

5. ማንኛውም የሚከናወን ተግባር መለኪያ እንዳለው እሙን ነው። ለምሳሌ ጦርነት በሚካሄድበት ጊዜ ድል (አመርቂ ሥራ እየተሰራ መሆኑ) የሚለካው በተገደሉ ወይም በተማረኩ ወታደሮች ልክ ፣ በቁጥጥር ሥር በዋሉ ቦታዎች ፣ በተደመሰሱ ወይም በተማረኩ የጦር መሳሪያዎች ወዘተ እንደሆነ ሁሉ የሰላማዊ ትግል ዋንኛ መለኪያው ወደትግሉ እያሳመነ በሚያመጣው ሰው ልክ ነው። በሌላ አነጋገር የዚህ ትግል ስኬት ዋንኛ መለኪያ «የጠላቶቼን ቁጥር በምን ያህል እየቀነስኩ የወዳጆቼን ቁጥር በምን ያህል እያበዛሁ ነኝ» የሚለው ነው። በተለይም ከተቃራኒው ወገን ወደዚህ የትግል መስመር እንዲቀላቀሉ ማሳመን የምንችላቸው ሰዎች መብዛት የትግሉን «ትርፋማነት» በግልጽ የሚሳይ መለኪያ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ስለዚህም በዚህ ትግል ውስጥ ያለን ሁሉ የትኩረት አቅጣጫችንን ወደዚህ አስተሳሰብ በማዞር ወደዚህ ትግል ማምጣት የምንችላቸውን ሁሉ ለማምጣት የሚቻለንን ማድረግ ይገባናል። በተለይም ከዚህ በፊት በጭንቅላታችን ውስጥ የተጠራቀመውን ጥላቻ ፣ የተሸናፊነት መንፈስ ፣ የበቀል ፍላጎት ፣ ወዘተ ወደጎን በማለት በጠላት ካምፕ ላይ ጥቃት በመሰንዘር የሚቻለንን ሰው ሁሉ ወደሰላማዊ ትግል በማምጣትና ወደፊት በመግፋት የትግሉን ተሳታፊዎች ቁጥር የማብዛቱን ኃላፊነት በብቃት መወጣት እንድንችል በአንክሮ ልናስብበት ይገባናል። ይህንን ተግባር እያሰፋነው በመሄድ በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ በቡድን ተደራጅቶ የሚገኝን ማንኛውንም አካል ወደፊት በምትመሰረተው ኢትዮጵያ በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ተባብረን መሥራት እንደምንችል የቅድሚያ ዝግጅት የምናደርግበትን መድረክ መክፈት እንችላለን። በተለይ ይህንን ሥራ ካሁኑ ከጀመርነውና በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ያለውን ጥያቄ በምንም መልኩ ይሆን እታገልለታለው ለሚለው ሕዝብ ለማስመለስ ከሚጥር ከማንኛቸውም ዓይነት ቡድን ጋር በአንድነት በመሆን የሁሉም ጥያቄ የተመለሰባትን አዲሲቱን ኢትዮጵያ ለመመሥረት የሚስችለንን ቀዳሚ ተግባር ከወዲሁ ለመጣል እንችላለን።

በመጨረሻም ባለፉት ዓመታት በአገራችን ላይ የተፈጸመውን ወደኋላ መለስ ብለን ስንመለከት ሕዝባችን ምን ያህል በዘር እንደተከፋፈለ መረዳቱ የሚያቅት ጉዳይ አይደለም። በጣም የሚያሳዝነው እንድንከፋፈል መንገዱን ያመቻቸልን የማፊያ ቡድን የሚሰራው ድርጊት አይደለም። እርሱማ የቃል ኪዳን ተግባሩ ስለሆነ በትጋት የሚያደርገው ነው። አሳዛኙ ተግባር ግን የእኛ ትዕዛዝ አክባሪነት እና የዘር ክፍፍሉን በትጋት ተግባራዊ ማድረግ ነው እንጂ። እስስካሁን የተሞኘነው ሊበቃን ይገባል። እስካሁን ክፍፍሉ ከፖለቲካ አልፎ እስከ አምልኮ ቦታዎች እንዲሁም ቤተሰብ ድረስ መዝለቁ ሊበቃው ይገባል። የኢትዮጵያን ቁስል በመጠገኑ ሂደት ላይ ማተኮርና ሥራውን ካሁኑ መጀመር አለብን። የዕርቅ መሠረት ካሁኑ ተጥሎ በሂደቱ ላይ ሁላችንም ተሳታፊ በመሆን ከግል ጀምረን ከዚያም ወደ ብሔራዊ ዕርቅ በመሸጋገር አገራችንን በማዳኑ ሥራ ላይ መረባረብ ይኖርብናል። በደቡብ አፍሪካ በኋላም በሞዛምቢክ አሁን ደግሞ በላይቤሪያ እየተካሄደ እንዳለው አይነት የሰላምና የዕርቅ ሥራ መሠረት ካሁኑ ተጥሎ ወደዚያ የሚያሸጋግረው ተግባር መከናወን መጀመር አለበት። የግድ በሥልጣን ላይ ያለው አካል እሺ እስከሚል መጠበቅ የለብንም። በተለያየ የፖለቲካ አመለካከት ተለያይተን ያለን ሁሉ እስቲ በመጀመሪያ ባንድ ጠረጴዛ ተሰብስበን የዚህን የዕርቅ ሃሳብ ዕቅድ እንንደፍ። ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ ይቻላል!! ምንም እንኳን ሕዝባችን በተለያዩ የዘር ፣ የሃይማኖት ወዘተ ጥላቻዎች ውስጥ እያለፈ ቢሆንም ሰሞኑን ለላይቤሪያው የሰላምና የዕርቅ ኮሚሺን ቃሉን እንደሰጠው የጎሳ መሪ በጦርነቱ ወቅት ለወታደራዊ ድል ለመብቃት ህጻናትን መስዋዕት ካደረገ በኋላ ልባቸውን እያወጣ ሲበላ እንደነበረውና ቢያንስ ለ**20,000** ላይቤሪያውያን ሞት ተጠያቂ እንደሆነ የሚነገርለት ይህ የአማጺያኑ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

መሪ[15] በቅርቡ ይፋ ወጥቶ ወንጀሉን ተናግሮ ቅጣቱ ለመቀበል ዝግጁነቱን እንደገለጸው ዓይነት የዕርቅና የፈውስ ዘመን ላገራችን ያስፈልጋታል:: ይህም መሆን ይችላል!! የዚህ ተግባር መሠረት ሲጣል በሕይወት ዘመናችን ካየን ምንም እንኳን ለፍጻሜው ባንደርስም፤ ምንም እንኳን ለድሉ መጨረሻ ባንበቃም እንደ ዶ/ር ኪንግ:-

> **". . . I'm not concerned about that now. I just want to do God's will. And He's allowed me to go up to the mountain. And I've looked over. And I've seen the Promised Land. I may not get there with you. But I want you to know . . . that we, as a people, will get to the Promised Land."[16]** ለማለት እንችላለን::

የወደፊቷ ኢትዮጵያ መሠረት ሲጣል ካሁኑ ካየን እና በዚያም ውስጥ እኛ የበኩላችንን ተሳትፎ እያደረግን ከሄድን አሁን ያለው ሁኔታ ብዙም አያሳስበንም:: አሁን ያለው አምባገነንና ከፋፋይ መንግሥት ብርታት አያስጨንቀንም ፤ ጭከናውም ተስፋ አያስቆርጠንም:: ተስፋ የቆረጥን ጊዜ ግን ይህንን የጋንዲን አነጋገር ሁልጊዜ በማሰብ በጽናት እንታገል::

«ተስፋ ስቆርጥ በታሪክ ውስጥ የእውነትና የፍቅር መንገድ ሁልጊዜ እንዳሸነፉ አስታውሳለሁ:: ጨካኞችና ነፍሰገዳዮች በዘመናቸው የማይበገሩ መስለው ሊታዩ ይችላል፤ በመጨረሻ ግን ያለጥርጥር ይሸነፋሉ - ይህንን ሁልጊዜ አስቡት::»

---

**The writer can be reached at mekbma@yahoo.com**

---

[15] http://news.bbc.co.uk/2/hi/africa/7200101.stm
[16] http://www.afscme.org/about/1549.cfm

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com